ActionDignity

Unrelenting Pursuit of Equity 20th Anniversary

# የሰራተኞች መገልገያ ሰነድ

WES MARIAM ASSEFA FUND










ቀውስ እና ወረርሽኝ የሰው ልጆችን የመብት ጥሰት ስጋት ከመፍጠርም በተጨማሪ ለነባሪ የሰው ልጆች መብት ጥሰት ተጋላጭነትን ያባብሳሉ። የዚህ አደጋ ተጠቂ የሆኑ ሰዎች ቁጥር በቅርብ አመታት ውስጥ እጅግ በትልቁ አድጓል። ይሄ ችግር ትኩረት ተሰጥቶት ካልታረመ በሰው ልጆች ህይወት ላይ የሚያመጣው ተፅእኖ የላቀ መከራን፡ የፍትህ መጓደልን እና ለአስጸያፊ ተግባራት ተጋላጭነትን ነው። ለዚህም ዋነኛ ተጠቂ የሚሆኑት የቀውስ ጊዜ አስፈላጊ ሰራተኞች እና የፊት መስመር ሰራተኞች ናቸው። ይህም አልበርታ በሚገኙ የስጋ ማሸጊያ ፋብሪካዎች ታይቷል። ስርአታዊ መሰናክሎች፡ ችግር ያለባቸው እና ለአደጋ የሚያጋልጡ የስራ ሁኔታዎች፡ ወረርሽኙ ባመጣው ተፅእኖ ምክንያት የስራ መተማመኛ አለመኖር እና ለጥቃት ተጋላጭነት፡ በስራ ቦታ እና በውጪም እየጨመረ የሄደው ዘረኝነት የመሳሰለው በተለይም በካርጊል እና በጄቢኤስ (JBS) ውስጥ በፍጥነት ጨምሮ ነበር። በኮቪድ 19 ምክንያት የመጣውን ቀውስ ማቅለል እና መከላከል ለብዙ ሃገራት እና የንግድ ኢንዱስትሪዎች ፈታኝ ሆኖባቸው ነበር። የመብት ጥሰቶችና በደሎች በተለይ ተጋላጭ በሆኑ እና በተገለሉ ቡድኖች ላይ የአካል እና አእምሮ ጭንቀቶች፡ ጉዳቶችን እና የስነልቦና ተፅእኖዎችን አስከትዋል። የአልበርታ የሰው ልጆች መብት ማስጠበቂያ ህግ ( Alberta Human Rights Act, AHR Act) በ12 መሰረታዊ ምክንያቶች በዘር፡ በቀለም፡ በዘር ግንድ፡ በትውልድ ስፍራ፡ በሃይማኖታዊ እምነት፡ በፆታ፡ በፆታ ማንነት፡ በፆታ መገለጫ፡ በእድሜ፡ በየአካል እና የአእምሮ ጤንነት መጓደል፡ በየትዳር ሁኔታ፡ በየቤተሰብ ሁኔታ፡ በየገቢ ምንጭ እና በየፆታ ዝንባሌ ላይ ተመስርተው የሚደረጉ የስራ ቦታ የማግለል መድሎዎችን ያግዳል።

**አሰሪዎች ሁሉንም በእኩልነት ያካተተ እና የሁሉንም የግል ክብር ያረጋገጠ የስራ ቦታ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። በአልበርታ የሰራተኞች መብት ማስጠበቂያ ህግ (ARH Act) መሠረት ሰራተኞች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው።**

1. ሁሉን በእኩልነት ያካተተ፡ የሰራተኞች ክብር የተጠበቀበት እና ከአግላይ መድሎ ነፃ የሆነ የስራ ቦታ የመስራት
2. ከአልበርታ የሰው ልጆች መብት ማስጠበቂያ ህግ ጋር በተገናኘ ስራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጓቸው ማናቸውም መሠረታዊ ሁኔታዎች ሁሉ መሟላት
3. ከአልበርታ የሰው ልጆች መብት ማስጠበቂያ ህግ ጋር የተቃረነ አግላይ መድሎ ተፈጽሞብናል ብለው ሲያምኑ ለአልበርታ የሰው ልጆች መብት ኮሚሽን (Alberta Human Rights Commission) ቅሬታን የማቅረብ

## መሰረታዊ የሰራተኞች መብት

**በካናዳ ያሉ ሰራተኞች በሙሉ ሶስት መሰረታዊ መብቶች አሏቸው**

1. የማወቅ
2. የመሳተፍ
3. ለአደጋ የሚያጋልጥ ስራን አልሰራም የማለት

**1. የማወቅ መብት**

**በስራዎ ቦታ እና በስራዎ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን በሙሉ የማወቅ እና እራስዎን ከአደጋዎች የመከላከል መብት አለዎት።**

**2. የመሳተፍ መብት**

**በስራዎ ቦታ በሚሰጡ የጤና እና ደህንነት ስልጠናዎች የመሳተፍ እና ለአደጋ አጋላጭ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን በተመለከቱ ጊዜ የመጠቆም መብት አለዎት።**

**3. ለአደጋ የሚያጋልጥ ስራን አልሰራም የማለት መብት**

**እርስዎንም ሆነ የስራ ባልደረባዎችዎን ለአደጋ የሚያጋልጥ ስራን አልሰራም የማለት መብት አለዎት።**



## ጠቃሚ ጥያቄዎች

### ከአደጋ እራስዎን ይጠብቁ

- አስፈላጊው ስልጠና ተሰጥቶዎታል?
- ስልጠናው የተቻኮለ እና ለመረዳት አስቸጋሪ ነበር?
- ለስራዎ አስፈላጊ የሆኑ አልባሳት እና የመከላከያ መሳርያዎች ተሟልተውሎታል?
- አደጋ በደረሰ ጊዜ ማድረግ የሚገባዎን ያውቃሉ?
- አሳሳቢ ጥያቄ ቢኖርዎ የሚያነጋግሩትን የስራ ቦታ ሃላፊ ያውቃሉ?

### ጤናዎን ይጠብቁ

- ጤንነት ይሰማዎታል ወይንስ የኮቪድ 19 የህመም ስሜት ይሰማዎታል?
- የመስሪያ ቤትዎን የመታመም ጊዜ ፖሊሲ ያውቃሉ?
- ስራ ቦታ በሽታን ለመከላከል የሚያስፈልገው ከሌሎች ጋር መራራቅ አለ?
- እንደ እጅን መታጠብ፡ ጭንብል መልበስን እና የስራ ቦታዎን ከጀርም የማጽዳት የመሳሰሉትን ጥንቃቄዎች ይወስዳሉ?

### የስራ ላይ ማስታወሻዎች

- ለአደጋ አጋላጭ የሆነ ነገር ከተመለከቱ ለሃላፊዎ ይጠቁሙ
- ስራዎ ለአደጋ አጋላጭ እንደሆነ ከተሰማዎት ወይንም የማግለል መድልዎ ከደረሰብዎት ለሃላፊዎ፣ ለስራ አስኪያጅ ወይንም ለስራተኞች አስተዳደር ያሳውቁ
- ስለ የስራ ቦታ መድልዎ እና ትንኮሳ እራስዎን ያስተምሩ። የአካልም ሆነ የስነልቦና ጥቃት ከስራ ባልደረቦችም፣ ከደንበኞችም ሊመጣ ይችላል
- የእርስዎ የአእምሮ ጤንነት አስፈላጊ ነው። ውጥረት በተሰማዎት ጊዜ፡ ጥቃት በደረሰብዎት ጊዜ እና ጭንቀት በተሰማዎት ጊዜ ለሌላ ሰው ያማክሩ

## የቀውስ ጊዜ አስፈላጊ ሠራተኞች መብት

እንደ የቀውስ ጊዜ አስፈላጊ ሰራተኛነትዎ በአልበርታ እና በካናዳ እርስዎን የሚካላከሉ ህጎች አሉ። በስራ ቦታ ያለዎትን መብት እና የአሰሪዎችን ግዴታ ማወቅዎ አስፈላጊ ነው።

### እንደሰራተኛ ያለዎት መብት

- ለእርስዎ እና ለስራ ባልደረባዎችዎ አደጋን ሊያስከትል የሚችል ስራን አልሰራም የማለት
- ለሰሩበት ስራ ክፍያን የመቀበል
- ስራዎን ያለአደጋ ለመስራት የሚያስችልዎ በቂ ስልጥና የማግኘት
- ከትንኮሳ ነፃ የሆነ የስራ ቦታ የመስራት
- ከአግላይ መድልዎ ነፃ የሆነ የስራ ቦታ የመስራት
- ፓስፖርትዎንም ሆነ የስራ ፈቃድዎን ከራስዎ ጋር የማቆየት
- ከአደጋ ነፃ የሆነ የስራ ቦታ የመስራት
- በስራዎ እና በስራ ቦታዎ ከባቢ ያሉትን አደጋዎች በሙሉ የማወቅ



**በስራ ቦታዎ ከአደጋ ነፃ ለመሆን ምን ማድረግ አለብዎ?**

- በእቅድ በተዘጋጁ የስራ ቦታ የጤንነት እና የደህንነት የስልጠና መርሃ ግብሮች ላይ መሳተፍ
- በስራ ቦታ ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን እና የስራ ልምዶችን መጠቆም እና ስለጠቆሙ አለመቀጣት
- የተመደቡበትን ስራ ጠንቅቀው ካላወቁ በቂው ስልጠና እንዲሰጥዎት መጠየቅ
- ስራዎን ከአደጋ ነፃ በሆነ መንገድ ለመስራት የሚያስፈልግዎትን አልባሳት መልበስና የመከላከያ መሳርያዎችን በአግባቡ መጠቀም
- የስራ ቦታ ፀብን ማስወገድ
- አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የስራ ልምዶችን መጠቆም

## በስራ ቦታዎ በአሰሪዎ ምን እንዲሟላልዎ ይጠብቁ?

**የአሰሪዎ ሃላፊነት**

- ለሰሩት ስራ የሚገባዎን ክፍያ መክፈል
- የስራ ቦታዎ ከአደጋ ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ
- ስራዎን ከአደጋ በነፃ ለማከናወን የሚያስፈልግዎትን የግል መከላከያ መሳርያዎችን እና አልባሳትን ማቅረብ
- በፅሁፍ የተዋዋሉትን የስራ ውል ማክበር

**አሰሪዎ ማድረግ የማይችላቸው ነገሮች**

- ያልተቀጠሩለትን ወይም በቂ ስልጠና ያልወሰዱበትን ስራ እንዲሰሩ ማስገደድ
- በህመም ወይንም በጉዳት ላይ ባሉበት ጊዜ ስራ እንዲሰሩ ማስገደድ
- ፓስፖርትዎንም ሆነ የስራ ፈቃድዎን መውሰድ እና ወስዶ ማቆየት
- ከካናዳ ወደሃገርዎ እንዲባረሩ (deport) ማስደረግ
- በካናዳ ያለዎትን የመኖርያ እና የስራ ፈቃድ ማስቀየር
- እርስዎን ለመቅጠር የወጣውን ማንኛውም ወጪ እርስዎ መልሰው እንዲከፍሉ ማድረግ

## ለተጨማሪ መረጃ

**የካናዳ የስራ ቦታ ጤና እና ደህንነት ማእከል**

Canadian Centre for Occupational Health and Safety – **www.ccohs.ca**

**የአልበርታ የሰው ልጆች መብት**

Alberta Human Rights **– www.albertahumanrights.ab.ca**

**በአልበርታ የህዝብ ህግ ማስተማርያ ማእከል**

Centre for Public Legal Education in Alberta **– www.cplea.ca/rightsatwork/10-rights-you-probably-didnt-know/**



**ጥቆማ**

ጥቆማው ወይንም ቅሬታው በስራ ቦታ የውስጥ ምርመራ ሊደረግበት ስለሚችል ወይንም ደግሞ መደበኛ የሰው ልጆች መብት ጥሰት ቅሬታ ሆኖ ለአልበርታ የሰው ልጆች መብት ኮሚሽን ሊቀርብ ስለሚችል የትንኮሳ ወይንም የማግለል መድሎ ቅሬታዎችን የሚያቀርቡ ሰራተኞች የተፈፀመባቸውን በደል እና የምስክሮችን ስም የጨመረ ዝርዝር ማስታወሻ መያዛቸው እጅግ አስፈላጊ ነው። በደል በተፈፀመም ጊዜ በደሉ ከተፈፀመበት ቀን በአንድ አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ቅሬታው ለአልበርታ የሰው ልጆች መብት ኮሚሽን መቅረብ ይኖርበታል።

ትንኮሳ የሚከሰተው አንድ ሰው ተቀባይነት ለሌለው የቃላት ልውውጥ ወይንም የአካል ንክኪ ሲጋለጥ ነው። በሌላ አገላለጽ ደግሞ አንድ ሰው በስራ ቦታ ሲበደል፤ የዛቻ ማስፈራራት ሲደርስበት፤ እንዲሳቀቅ ሲደረግ ወይንም ጥቃት ሲደርስበት ነው። ይሄ ደግሞ በአልበርታ የሰው ልጆች መብት ማስጠበቂያ ህግ የተከለከለ ነው። ሶስቱ የስራ ቦታ ትንኮሳዎች የቃላት ወይንም የፅሁፍ፡ የምስል ወይንም እይታ እና የአካል ናቸው።

በካናዳ ህግ ሁሉም ሰራተኞች መብታቸው የተጠበቀ ነው። በካናዳ የጊዜያዊ የውጪ ዜጋ ሰራተኞች (Temporary Foreign Workers, TFW) መበደል ጥብቅ ጉዳይ ሆኖ ይወሰዳል። ፕሮግራሙን ያለአግባብ የሚጠቀሙም ሆነ ሰራተኞችን የሚበድሉ አሰሪዎች ቅጣት ይከፍላሉ ወይንም በፕሮግራሙ እንዳይሳተፉ ይታገዳሉ።

**ጥቆማን ሲያቀርቡ ማወቅ የሚገቡዎ ነገሮች**

- የተቻለውን ያህል ብዙ መረጃን ማቅረብ በጣም አስፈላጊ ነው።
- የሚያቀርቡት ማንኛውም መረጃ በካናዳ የግላዊነት ህግ (Canada Privacy Law) የተጠበቀ ነው።
- መንግስት ለአሰሪዎም ሆነ ለማንኛውም የስራ ባልደረባዎ ጥቆማውን ማን እንዳቀረበ አያሳውቅም።
- ጥቆማን ለማቅረብ ስምዎንም፡ ስልክ ቁጥርዎንም ሆነ የስራ ፈቃድዎን (LMIA) ማሳወቅ አይጠበቅብዎትም።
- ያለፈቃድዎ ማንም ሊያነጋግርዎት ወይንም የእርስዎን መረጃ ሆነ ማስረጃ ለማንም ሊያጋራ አይችልም።
- ለግላዊነት ህግ ምክንያት ሲባል የጥቆማዎ የሂደት ደረጃ አይነገርዎትም።

**ጥቆማን ለማቅረብ የሚያስፈልጉ መረጃዎች**

- የድርጅቱ ወይንም የንግድ ተቋሙ ስም፡ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች ስም እና የስራ ድርሻቸው
- የሚጠቆመው በደል ምን እንደሆነ

**የተለያዩ የመጠቆሚያ መንገዶች**

- በስልክ
- በአካል በመገኘት
- በደብዳቤ

የሰው ልጆች መብት የተፈጥሮ መብት ሲሆን የሲቪል መብት ግን የአንድ የፖለቲካ ግዛት ወይንም ሃገር ህጋዊ አባል በመሆን የሚገኝ መብት ነው። የአግላይ መድሎ ሰለባነት የሚመጣው አንድ ሰው መጥፎ ሲያደርግብዎ ወይንም ደግሞ አግላይ መድሎን በመቃወም ቅሬታን ማቅረብዎም ሆነ ሌላ የአግላይ መድልዎ የደረሰበትን ሰው መርዳትዎ ለትንኮሳ ሲያጋልጥዎ ነው።



# HELPLINES IN ALBERTA

### Basic Needs, Labor Issues, Accessing Community Resources

**Basic Information & Referral System**
211 (24/7)

**Cargill Food Union Representative, High River**
Joe Attwood & Devin Yeager
1-888-468-6466

**ActionDignity**
915 33 St., NE, Calgary, AB T2A 6T2 │ Phone: 403-263-9900
www.actiondignity.org

**Migrante Alberta**
403-392-8286
www.migrantealberta.ca/

### Legal Counseling & Information, Human Rights, Basic Needs, Health Care

**Worker Resource Center**
440 - 999 8th St., SW Calgary, AB T2R 1J5
403-264-8100
www.helpwrc.org/

**Alberta Civil Liberties Research**
2500 University Drive, NW, Calgary, AB T2N 1N4
403-220-2505
www.aclrc.com/navigating-the-legal-system

**Women's Centre of Calgary**
39 4 St., NE, Calgary, AB, T2E 3R6
403-264-1155
www.womenscentrecalgary.org

**Calgary Immigrant Women's Association**
200 - 138 4 Ave., SE, Calgary, AB T2G 4Z6
403-263-4414
www.ciwa-online.com

### Settlement, Newcomers, Immigrants, Refugees, Job Search, Employment & Language Training

**Centre for Newcomers**
125 - 565 36 St., NE, Calgary, AB T2A 6K3
403-569-3325

**The Immigrant Education Society (TIES)**
3820 - 32 St., NE, Calgary, AB T1Y 7L9
403-291-0002 │ 403-235-3666
www.immigrant-education.ca

**Calgary Bridge Foundation For Youth (CBFY)**
203 - 602 11 Ave., SW, Calgary, AB T2R 1M7
403-230-7745
www.cbfy.ca

### Financial, Jobs Search, Homelessness, Seniors

**Alberta Supports (Alberta Income Support)**
Toll-Free 1-877-644-9992 (In Alberta)
TTY 1-800-232-7215 Toll-free in Alberta
TTY 780-427-9999 Edmonton

**Alberta Works Centre**
9499 137 Ave., NW, Edmonton, AB T5E 5R8
780-422-9440

### Health and Mental Wellness

**Distress Centre of Calgary (24-hour crisis line)**
999 8th St., SW, Calgary, AB T2H 1J5
403-266-HELP (4357)


**Alberta Supports**
Call Alberta Supports: Help is available in more than 100 languages
Call between 7:30 am to 8 pm (open Monday to Friday, closed statutory holidays)
Toll free: 1-877-644-9992 (in Alberta)
TTY – ask to speak to Alberta Supports.
TTY: 1-800-232-7215 toll free (in Alberta)
TTY: 780-427-9999 (Edmonton)
www.alberta.ca/alberta-supports.aspx

**Athabasca Alberta Supports Centre**
3rd Floor Duniece Centre, 4810 50 St., Athabasca, Alberta T9S 1C9
780-675-2243
www.css.athabascado.gov.ab.ca

**Barrhead Alberta Supports Centre**
Provincial Building, 6203 49 St., Barrhead, Alberta T7N 1A4
780-674-8345
www.css.barrheaddo@@gov.ab.ca

**Bonnyville Alberta Supports Centre**
5401 44 St., Bonnyville, Alberta T9H 2G3
780-826-4175
www.css.bonnyvilledo@gov.ab.ca

**Brooks Alberta Supports Centre**
200 - 600 Cassils Road East, Brooks, AB T1R 1M6
403-362-1278
www.css.southreg@gov.ab.ca



# HELPLINES IN ALBERTA


## Health and Mental Wellness (CONT.)

**Calgary Central-Lancore Alberta Supports Centre**
Main Floor Lancore Building, 1021 10 Ave., SW
Calgary, AB
403-297-2094
www.css.ds-calgary@gov.ab.ca

**Calgary East - Westland Alberta Supports Centre**
Main Floor Westland Professional Centre
2752 Sunridge Way, NE , Calgary AB, T1Y 0A5
403-297-1907
TTY 1-800-232-7215
www.ds-calgary@gov.ab.ca

**Calgary North - One Executive Place Alberta Supports Centre**
1816 Crowchild Trail NW, Calgary, AB T2M 3Y7
403-297-7200
www.css.ds-calgary@gov.ab.ca

**Calgary South - Heritage Square Alberta Supports Centre**
403-297-2020
www.css.heritage@gov.ab.ca



የBRAVE Worker’s ፕሮግራም

(**BRAVE** ምህፃረ ቃል ሲሆን ትንታኔ ትርጉሙም በየአስፈላጊ ሠራተኞች መብት እና አስፈላጊነት ማመን ነው)

WES MARIAM ASSEFA FUND

የፕሮግራሙ አላማ በስጋ ማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ የዘር መድሎ ተጠቂ የሆኑ አስፈላጊ ሰራተኞችን ፈተናዎች እና መሰናክሎች በማጉላት እና መፍትሄ በመፈለግ የሰው ልጅ መብቶቻቸው እና የሰራተኛ መብቶቻቸው መከበራቸውን ማረጋገጥ ነው። BRAVE Workers ህብረተሰቡ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት፡ የሠራተኛ ቡድኖች እና ማህበራት፡ የአግልግሎት ሰጪ አካላት እና የመንግስት አካላት ጋር የሚያደርገው የቀጠለ ግንኙነት ላይ በኮቪድ 19 ምክንያት በደረሰው የስርዓት ለውጥ የተባባሰውን ኢፍትሃዊነት ለመቀነስ መንገድን በመጥረግ ያግዛል።


**Credits:**

- Amaka Agonsi, Catamount Fellowship for Emerging Changemakers, Mount Royal University
- Marilou Roxas, Community Support Workers Program, AGA Academy
- Juanito Gegajos, The Immigrant Education Society
- BRAVE Workers project team, ActionDignity


**Sources:**


- Alberta Human Rights -https://albertahumanrights.ab.ca/
- 10 Rights at Work You Probably Didn’t Know You Have in Alberta - https://www.cplea.ca/rightsatwork/10-rights-you-probably-didnt-know/
- Canadian Centre for Occupational Health and Safety -https://www.ccohs.ca/
- Fronteirs -https://www.frontiersin.org/
- Our work on human rights in humanitarian action, United Nations, Workers Rights https://www.ohchr.org/en/humanitarian-crises/our-work-human-rights-humanitarian